ላትቪያ

# የእርስዎ የግል መረጃ ወደ ዩሮዳክ (EURODAC) የሚተላለፈው ለምንድን ነው?

አይነት ኤፍ (Type F)

**በአውሮፓ ህብረት ዳግም ማስፈር እና የሰብአዊ መግቢያ ማዕቀፍ ሥር የመግቢያ ሂደትን ለማካሄድ የተመዘገቡ ሰዎች**



AMHARIC

## ይህን በራሪ ወረቀት ለምን እየተቀበልኩ ነው?

ወደ አውሮፓ ህብረት (EU) አባል አገር ለዳግም ማስፈር ወይም ሰብአዊ መግቢያ እየተመረመሩ ነው።

ይህ በራሪ ወረቀት በባለሥልጣናት ስለሚቀመጠው መረጃ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቀመጥ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል።

## ዳግም ማስፈር እና ሰብአዊ መግቢያ ምንድን ነው?



ወደ አውሮፓ ህብረት አባል አገር ለዳግም ማስፈር ወይም ለሰብአዊ መግቢያ እየተመረመሩ ነው። ይህ ማለት የእርስዎ ጉዳይ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲ (United Nations Refugee Agency፣ UNHCR) ወይም በሌላ ተዛማጅ ተቋም ተገምግሟል ማለት ነው።

አሁን ከእነዚህ የአውሮፓ ህብረት አባል አገራት አንዱ እርስዎን በዛች አገር ውስጥ እንዲኖሩ ለመቀበል እና ዓለም አቀፍ ጥበቃ ወይም ሰብአዊ ጥበቃ ሁኔታ ለመስጠት መስማማት አለመስማማታቸውን ይወስናሉ።

## የጣት አሻራዬን እና ፎቶግራፌን መስጠት ያለብኝ ለምንድን ነው?

በዚህ አገር ያሉ ባለሥልጣናት የጣት አሻራዎን እና ፎቶግራፍዎን ይወስዳሉ።
ይህ መረጃ፣ ከማንነትዎ መረጃ እና ከሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ጋር፣ ወደ ዩሮዳክ (Eurodac) የመረጃ ቋት ይተላለፋል።

ዩሮዳክ የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገር ዜጎች ያልሆኑ የተወሰኑ የሰዎች ምድቦችን ልዩ የጣት አሻራ እና የፎቶግራፍ ስብስባቸው ጋር ያገናኛል።

ይህ የመረጃ ቋት መረጃዎን ማየት በሚችሉ 31 የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገሮች ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

የሚከተሉትን ያጣራሉ፡

- በአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገር ውስጥ አስቀድሞ ትክክለኛ የጥበቃ ሁኔታ ካለዎት
- በአውሮፓ ህብረት አባል አገር ለዳግም ማስፈር ወይም ለሰብአዊ መግቢያ አስቀድሞ ተቀባይነት ካገኙ
- ማመልከቻዎ ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ በደህንነት ምክንያት በአውሮፓ ህብረት አባል አገር ውድቅ ከተደረገ
- ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ ወደ አውሮፓ ህብረት አባል አገር ለመግባት ፈቃድዎን ካልሰጡ ወይም ፈቃድዎን ካነሱ።

መረጃዎን የሚመዘግበው የአውሮፓ ህብረት አባል አገር በመጀመሪያ ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ አንዳቸውም በእርስዎ ላይ ተፈጻሚ መሆናቸውን ብቻ ያጣራል። በዚህ ደረጃ፣ የእርስዎ መረጃ በዩሮዳክ (Eurodac) ውስጥ አይቀመጥም።

**አሁን በላትቪያ ውስጥ ነዎት፣ እሱም የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገር ነው።**
**የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች የሚከተሉት ናቸው፡**

27 የአውሮፓ ኅብረት (EU) አባል ሀገራት፡- ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሳይፕረስ፣ ቼኪያ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ ጣሊያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ የአየርላንድ ሪፐብሊክ፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፔን፣ ስዊድን እና

4 ሌሎች ሀገራት፡- አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድ።

# በዩሮዳክ (EURODAC) ውስጥ ምን መረጃ ይቀመጣል?



የሚከተለው መረጃ ሁልጊዜ ይቀመጣል:

- የጣት አሻራዎችዎ
- ፊትዎን የሚያሳይ ፎቶግራፍ
- አሁን የሚጠቀሙባቸው ወይም ቀደም ሲል የተጠቀሙባቸው ሁሉም ስሞችዎ
- የትውልድ ቀንዎ
- የትውልድ ቦታዎ
- ዜግነትዎ ወይም ዜግነቶችዎ
- ጾታዎ
- የተጠቀሙባቸው የማንነት ወይም የጉዞ ሰነዶች ቅጂዎች፣ ካሉ፣ ትክክለኛነታቸውን የሚመለከት መረጃን ጨምሮ
- የጣት አሻራዎትን እና ፎቶግራፍዎን የወሰደው የባለሥልጣኑ የተጠቃሚ መለያ (user ID) እና መረጃዎ የተወሰደበትና የተላለፈበት ቀናት
- ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያመለከቱበት አገር
- ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያመለከቱበት ቀን።

የሚከተለው መረጃ አስፈላጊ ከሆነ በዩሮዳክ ውስጥ ይቀመጣል:

- ማመልከቻዎን ለመመርመር ሃላፊነት ያለው አገር
- ከተዛወሩ፣ የሚዛወሩበት የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገር
- ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ እና በአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገሮች ውስጥ የመቆየት መብት ከሌለዎት
- ማመልከቻዎ በድንበር ሂደት ውስጥ ታይቶ ውድቅ ከተደረገ ወይም ማመልከቻዎ እንደተሰረዘ ከተቆጠረ
- በአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገር የተሰጡዎትን ማንኛውንም ቪዛዎች በተመለከተ መረጃ
- የአውሮፓ ህብረት ፕላስ (EU+) አገሮች ክልልን ለቀው የወጡባቸው ማናቸውም ጊዜያትን የተመለከተ መረጃ
- ወደ ትውልድ አገርዎ በፈቃደኝነት ለመመለስ የቀረበልዎትን ጥያቄ እንደተቀበሉ ወይም እንዳልተቀበሉ የሚገልጽ መረጃ።

በዩሮዳክ ውስጥ የተቀመጠ ትክክል ያልሆነ መረጃን የማግኘት እና የማስተካከል መብት አለዎት እንዲሁም መረጃዎ በህገ-ወጥ መንገድ ከተያዘ እንዲሰረዝ የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህንን ለማድረግ የመረጃ ተቆጣጣሪውን ማግኘት ይችላሉ። የመረጃ ተቆጣጣሪው የእውቂያ ዝርዝሮች **'ሌላ መረጃ በዩሮዳክ (Eurodac) ውስጥ ይቀመጣል?'** በሚል ርዕስ ባለው በራሪ ወረቀት ውስጥ ማግኘት ይችላሉ።

## የእኔ የግል መረጃ በዩሮዳክ (EURODAC) ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ይቀመጣል?



እንደ ውሳኔው አይነት ይለያያል ነገር ግን የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡

- መረጃውን የሚመዘግበው አገር እንዲገቡ ከፈቀደ 5 ዓመታት፣ ወይም
- መረጃውን የሚመዘግበው አገር በደህንነት ምክንያት ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ 3 ዓመታት፣ ወይም
- ለመግባት ከእንግዲህ እንደማይፈልጉ ከወሰኑ ወይም ባለሥልጣናት ባለመተባበርዎ ምክንያት እንዲህ ብለው ካመኑ 3 ዓመታት።

ይህ ጊዜ ከማለቁ በፊት ዜግነት ካገኙ፣ መረጃዎ ይሰረዛል። መረጃዎ ከተሰረዘ፣ ዜግነት ባገኙበት አገር ያለዎትን ሁኔታ አይነካም።

ይህ ማስታወሻ ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። ይህ ማስታወሻ ሊውልበት ስለሚችል ጥቅም የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅትም (EUAA) ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025